**ዓለም አቀፍ የአማራ ኅብረት**
11303 Amherst Avenue, Suite 2
Silver Spring MD, 20902

መስከረም 14, 2013 ዓ/ም

# በህወሀትና ኦነግ እንዲሁም የዉጭ ኃይሎች አቀነባባሪነት በኦነግ ሸኔና በጉምዝ ታጣቂዎች በመንግሥት መዋቅር በመታገዝ በአማራና በአገው ተወላጆች፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ያደረሱትን እጅግ ዘግናኝና ኢሰባዊ የሆነ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(Genocide) አጥብቀን እናወግዛለን።

ከጳጉሜ አንድ 2012 እስከ መስከረም ሦስት 2013 ዓ/ም በመተከል ዞን፣ በቡለን ወረዳ፣ አጃር ቀበሌና በወምበራ ወረዳ መልካን ቀበሌ የኦነግ ሸኔና የጉምዝ ታጣቂዎች በክልሉ የመንግሥት መዋቅር በመታገዝ በአማራና አገው ተወላጆች ላይ እጅግ ዘግናኝና ፍጹም ጭካኔ የተሞላበት የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(Genocide) ፈጽመዋል። ከጭፍጨፋው የተረፉ የዐይን እማኞች እንደተናገሩት እነዚህ ሽብርተኞች ሊገድሏቸው ያሰቧቸውን ሰዎች አስቀድመው የስም ዝርዝር አዘጋጅተው ይዘው እንደነበረ ነው።

ለጭፍጨፋው ምክንያት የሆነውም ለምን ወደአገራችሁ አትሄዱም፡ አገራችንን፣ መሬታችንን ልቀቁ በሚል ነው። በዚህ ጭፍጨፋ ከ160 በላይ የሚሆኑ አማራዎች፣ አገዎችና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በአስቃቂ ሁኔታ የተገደሉ ሲሆን በሽዎች የሚቆጠሩ ተፈናቅለዋል፤ ሀብት ንብረታቸውም ተዘርፏል። በዚህ አሰቃቂ ወንጀል ፍጹም አረመኒየያዊ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ከተጨፈጨፉት ውስጥ የ 3 ዐመት ህጻንና ሴቶች ይገኙበታል። ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ወጣት ሴቶችም በአሸባሪዉ ቡድን ታግተው ተወስደዋል። ለመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ይህንን የመሰለ ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሲካሄድ መንግሥት አለ ለማለት ያስችላልን?

‘**ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት**’ በመተከል፣ ቡለንና ምበራ ወረዳዎች በአማራና አገው፣ ኦርቶዶክስ ኢትዮጵያዊያን የደረሰውን ዘግናኝ የዘር ማጥፋት(Genocide) ወንጀል አጥቦቆ ያወግዘዋል። ጨፍጫፊዎችም ተጠያቂ እንዲሆኑ አጥብቆ ይሠራል።

በነገራችን ላይ በመተከል የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(Genocide) ባለፈው ሰኔ ወር በኦሮሚያ ክልል በአማራዎችና በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ ከተፈጸመው ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ(Genocide) ጋር በጣም ተመሳሣይ ነው። በሰኔው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ የተፈጸመው ቀደም አድርጎ ማን ማን እንደሚገደሉ የሚያሳይ የስም ዝርዝር ተይዞ አማራውና የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታዩን በመለየት ነበር፣ እንዲሁም አቅም ያላቸውን ባለሀብቶችና ቤተክርስቲያንን የሚደግፉ ምእመናንን በመለየት ጭምር ነበር። አሁን መተከል ውስጥም የተፈጸመው ጭፍጨፋም እንደዚሁ ሀብት ያላቸውንና ጥሩ አቅም ያላቸውን በመለየት ነው። በሰኔ ወር በኦሮሚያ ክልልም ሆነ ባሁኑ የመተከል ጭፍጨፋ የፈጸሙት ተመሳሳይ የሆኑ ኃይሎች ሲሆኑ የመንግሥት መዋቅርም በሁለቱም የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋዎች ተባባሪ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ።

መተከል የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ወንጀል አሁን የመጀመሪያው አይደለም፡ ቀደም ሲልም በተደጋጋሚ ጊዜ ተፈፅሟል፡ ዋናው ጥያቄ ለምንድን ነው ሠላማዊ የነበረው መተከል ያማራውና የአገው ተወላጆች የሲኦል ቦታ የሆነው? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ እስኪ ስለመተከል ጥቂት እንበል፦

ከ 1983 ዓ/ም በፊት መተከል በምዕራብ ጎጃም ሥር የሚገኝ አንድ አውራጃ ነበር። አማራውን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለማዳከም ዐላማዋ አድርጋ የተነሳቸው ህወሀት ወልቃይት፣ ጠገዴን፣ ጠለምትን፣ ሁመራን ከጎንደር፣ ራያን ከወሎ በጉልበተ ለራሷ ስትወስድ፣ መተከልን ከጎጃም፣ አሶሳን ከወለጋ በመውሰድ አንድ ላይ “ቤንሻንጉል-ጉምዝ” የሚል ኪልል ፈጠረች። መተከል የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል አንደኛው ዞነ ሆነ። መርዘኛ የሆነውን የህወሀት ህገመንግሥት መነሻ አድርጎ የተቀረጸው የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ህገመንግሥት፣ አንቀጽ 2 እንደሚለው በክልሉ ለሚኖሩ ሁሉም ብሄረሰቦች ዕውቅና ቢሰጥም፣ የክልሉ ባለቤትነት የተሰጠው ለበርታ፣ ጉምዝ፣ ሺናሻ፣ ማኦና ባኩ ብሄረሰቦች ብቻ ነው። እንግዲህ በቁጥር ብዛት ያላቸው አማራና አገዎች ቢሆኑም፣ በክልሉ መኖር የሚችሉት ከላይ የተጠቀሱት 5 ብሄረሰቦች እስከፈቀዱ ድረስ ነው ማለት ነው።

መተከል በጣም ለምና በተፈጥሮ ማዕድን የታደለ ቦታ ነው። መተከል ያለው ለም የሆነ የእርሻ መሬት በዘመናዊ ግብርና ዘዴዎች ቢያዝ እንኳንስ ኢትዮጵያን አፍሪካን መመገብ የሚችል ነው። በፊት የተጀመሩት የጣና በለስ ፕሮጀክቶችም ሆነ አሁን የሚሠራው የዓባይ ህዳሴ ግድብ የሚገኘውም እዚሁ መተከል ውስጥ ነው። መተከል እጅግ ጠቃሚ የሆነች የጅኦፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥፍራ ነች። አማራውን ከሱዳን ጋር የምታዋስነውም ነበረች።

ህወሀት የቤኒሻንጉል ጉምዝን ክልል ያዋቀረችበት ምክንያት፣ 1) አማራውን ወደውጭ መውጫ ለማሳጣት፣ 2) መተከል የሚሰጠውን የኢኮኖሚ አቅም ከአማራው ለመንጠቅ፣ 3) ደብቃ በያዘችው ካርታ መሠረት ትግራይን ከቤንሻንጉል ጋር ለማያያዝና ብሎም የግድቡን ቦታ ለመቆጣተር ነበር። ፡ አሁን ደግሞ ባለተራ ነኝ ብሎ የሚያስበው የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይል ሁሉንም ነገር ከህወሀት መገልበጥ ሙያው አድርጎ ስለያዘው መተከልን፣ ብሎም የዓባይን ግድብ ወደራሱ ሥር ለማስገባት፣ ባለቤትና ባለርስት የሆነውን አማራውንና አገውን በመጨፍጨፍ፣ ከጭፍጨፋው የተረፈውንም እንዲፈናቀል በማድረግ መስፋፋቱን ቀጥሎበታል። ይህንን መሰል ተመሳሳይ ድርጊት በኦሮሚያ ክልል በሚኖሩ አማሮችና የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ እየፈጸመ እንደሚገኝ ከላይ ተገልጿል፡፡ የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች ስንል ሁሉንም ማለታችን ሲሆን የኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲንም የሚያጠቃልል ነው። ሁሉም የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች መተከልን በተመለከተ ያላቸው ዕቅድ ምን እንደሆነና ምን እየሠሩ እንደሆነ በድብቅ ተቀርጾ በመውጣት ለህዝብ ይፋ የሆነው የአቶ ሺመልስ አብዲሳ ንግግር ያረጋግጥልናል፡፡ አቶ ሺመልስ፣ ቤንሻንጉል ውስጥ አማርኛ እየሞተ ነው፣ በምትኩ ኦሮሞኛ ወደ37% እንዲነገር ተደርጓል ነው ያለው፡፡ ይህም ማልት አማራውና ኣገው ይገደላል፣ ከግዲያ የተረፈው ይፈናቀላል፣ በምትኩ ኦሮሞውችን ያሰፍራሉ፣ እንዲሁም ሁሉም ኦሮሞኛ እንዲማር ይገደዳል ማለት ነው።

ይህ አማርውንና አገውን እንዲሁም የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን በመጨፍጨፍ የተጠመደው ኃይል የእርስ በርስ መተላለቅን የሚፈጥር ጦርነት ለመጀመሩ ምክንያት እንዳይሆን ቆም ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት እንላለን። እንዲሁም ኢትዮጵያን እንዲያስተዳድር የተረከበው የፌደራል የበላይ አካል፣ የመንግሥት መዋቅር በጭፍጨፋው እየተሳተፈ ስለሚገኝ የዘር ጭፍጨፋ ኣልተካሄደም እያለ ለማስተባበል ወይም ወንጀሉን ለመደበቅ ከመሯሯጥ፣ የወንጀሉ አካል መሆኑን ተገንዝቦ አስቸኳይ

ዕርምጃ በመውሰድ የመከላከያ፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የህዝብ ደህንነት፣ በሙሉ የፀጥታ አካላትና የፍትሳ ሥርዓቱ ላይ አዲስ ሪፎረም በማካሄድ ኢትዮጵያውያንን በብሔር ኮታ ሳይሆን በችሎታ የሃላፊነት በታዎችን እንዲይዙ ማደረግ አለበት።

በጣም የሚገርመው ነገር፣ በተደጋጋሚ ዜጎች ከተጨፈጨፉ በኋላ በመድረስ የመከላከያ ሠራዊት ገብቼ አረጋጋሁ የሚልበት ምስጢር ምን እንደሆነ ለመገንዘብ የሚያዳግት ቢመስልም በእኛ እምነት፣ በአንድ ብሔር የበላይነት የተያዘው የመከላከያ አመራር፣ አማራውና ኦርቶዶክሱ እንዲጨፈጨፍ ሆን ብሎ ተባባሪነቱን እያሳዬ መሆኑን ነው።

በመተከል ውስጥ በአማሮችና በአገዎች ላይ ለደረሰው የዘር ጭፍጨፋ(Genocide) ዋነኛ ተጠያቂዎች ህወሀትና ኦነግ ቢሆኑም፣ የግብፅም ረጅም እጅ እንዳለበት ምንም ጥርጥር የለንም። ከሁሉም በበለጠ፣ የዜጎችን የመኖር ዋስትና ማስጠበቅ ባለመቻሉ በዶ/ር ዓብይና በአቶ ደመቀ መኮንን የሚመራው የፌደራል መንግሥትና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግሥት በቅድሚያ ተጠያቂዎች ናቸው። እንዲሁም በቅርብ እርቀት መተከል የሚኖሩትን የአማራና የአገው ተወላጆችን ህይዎት መታደግ ያልቻለው ወይም የማይፈልገው የአማራ ክልላዊ መንግሥት ከዓይነተኛ ተጠያቂዎች ውስጥ አንዱ ነው።

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ለመንግሥት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀርባል፣

፩ኛ/ የዘር ጭፍጨፋውን የሚመረምር ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን በአስቸኳይ ተዋቅሮ ምርመራ እንዲጀመር አጥብቀን እንጠይቃለን፤

፪ኛ/ ጭፍጨፋውን የፈጸሙትም ሆነ የተባበሩት የመንግሥት አካላት በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ፤

፫ኛ/ በጭፍጨፋው ለተጎዱት፣ ለቆሰሉት፣ ንብረት ለተዘረፈባቸው ተገቢው ካሣ እንዲደረግ፤

፬ኛ/ የክልሉን ፀጥታና የህዝብ ደህንነት ዋስትና ማስጠበቅ ያልቻለው የቤንሻንጉል ጉምዝ አመራር በተለይም የመተከል ዞን አመራሮች በአስቸኳይ ከሥልጣን እንዲነሱ፤

፭ኛ/ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ ህገመንግሥት በአስቸኳይ ታግዶ በምትኩ የሁሉንም የክልል ነዋሪዎች እኩልነት የሚያረጋግጥ ህገ መንግሥት እንዲቀረፅ እንጠይቃለን፤

፮ኛ/ በክልሉ ውስጥ በሁሉም የሥልጣን ተዋረዶች በተለይም በፀጥታ መዋቅሩ ውስጥ ሁሉም ብሔረሰቦች የተካተቱበት ሆኖ እንዲዋቀር እንጠይቃለን፤

፯ኛ/ የቤንሻንጉል ጉምዝ ልዩ ኃይል በተደጋጋሚ አድሏዊነት በማሳየት የአማራዎችንና አገዎችን ህይዎት መታደግ ባለመቻሉና፣ ቢችልም ስለማይፈልግ ከአማራው ክልል ልዩ ኃይል የተወሰነ ቁጥር ተልኮ ጥበቃ እንዲያደርግላቸው እንጠይቃለን፤

፰ኛ/ የአማራ ብልፅግና ፓርቲ የበላይ አመራሮች እንወክለዋለን የሚሉትን የአማራ ህዝብ በኦሮሚያ ክልልና በቤንሻንጉል ጉምዝ በተለይም በመተከል ዞን ይህንን ያህል ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ዘመቻ (Genocide) ሲካሄድ የመከላከል ሥራ ባለማድረጋቸው፣ እንዲያውም ይባስ ብሎ ጭፍጨፋውን ከሚያካሂዱት ጋር ወግነዉ በመቆማቸው ከሥልጣናቸው በአስቸኳይ ተነስተው፣ ህዝቡን ለመታደግ በሚችሉ አዲስ አመራሮች እንዲተኩ አጥብቀን እንጠይቃለን፤

በተለይም አቶ ደመቀ መኮንን የሥጋ ዘመዶቹ ጭምር በሚገኙበት መተከል ህዝቡ በግፍ በተደጋጋሚ ሲታረድ ዝም ብሎ በማየት ከሥልጣነ መንበሩ ላይ ተደላድሎ መቀመጡ እጅግ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን ከልክ በላይ አስተዛዛቢ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም በርሱ የሚመራው የአማራ ብልፅግና ፓርቲ፣ ማለትም የቀድሞው ብአዴን/አዴፓ፣ የበላይ አመራሩ ይዋል ይደር ሳይባል ከቦታው መወገድ አለበት።

፱ኛ/ ባለፉት ሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ በዶ/ር ዓብይና በአቶ ደመቀ መኮንን የሚመራው የፌደራል መንግሥት ዋነኛ ሃላፊነቱን፣ ይኸውም የዜጎችን በህይዎት የመኖር መብት ማስጠበቅ ስለተሳነው፣ በመከላከያና በፀጥታ መዋቅሩ ዉስጥ ያሉ ከአንድ ብሔር (ኦሮሞ) የተወጣጡ አመራሮች

ከቦታቸው ተነስተው ብቃት ባላቸውና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሚወክሉ አዳዲስ አመራሮች እንዲተኩ እንጠይቃለን።

# ለህዝብ የቀረበ ጥሪ

፩ኛ/ የአማራ ብልፅግና ፓርቲ የመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ አመራር አባላት በሀገራችን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን አስጨናቂ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት አማራውን አገውንና ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑን ከዕልቂት ለማዳን የሚያስችል ሥራ እንድትሠሩ አጥብቀን እንጠይቃለን፣

፪ኛ/ በአማራ ክልል ውስጥ የምትኖሩ አማሮች፣ አገዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ክርስቲያንና ሙስሊም ብላችሁ ሳትለያዩ፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በሸዋና በጎጃም በሁሉም በኩል በህወሀትና ኦነግ በግብፅ በመታገዝ የተከፈተባችሁን ያልታወጀ ጦርነት ለመከላከል ቁርጣችሁ መነሳት እንዳለባችሁ እናስገነዝባለን፤

፫ኛ/ ከአማራው ክልል ውጭ የምትኖሩ አማሮች፣ መላው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዕምነት ተከታዮች፣ መጪው ጊዜ በጣም አስከፊ መሆኑን ተገንዝባችሁ፣ ዐይናችሁ እያዬ ዝም ብላችሁ ከማለቃችሁ በፊት ለመከላከል የሚያስችላችሁን አደረጃጀት በአስቸኳይ እንድትፈጥሩ ጥሪ እናቀርባለን። በተጨማሪ፣ መንግሥት ይመጣልናል ወይም ይጠብቀናል ብላችሁ መዘናጋት እንደሌለባችሁ ለማስገንዘብ እንወዳለን። እየሆነ ያለውን ሁሉ በግልፅ ስለምታውቁት ለእናንተ መንገር ለቀባሪው አረዱት ነው የሚሆነው።

፬ኛ/ ግብፅ፣ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የህዳሴ ግድብም ሆነ ሌሎች በዓባይ ዙሪያ ሊሠሩ የታቀዱ ፕሮጀክቶች ዕውን እንዳይሆኑ ከውስጥ ባንዳውች ጋር በመቀናጀት፣ በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰች ያለውንና ወደፊትም ልታደርስ የምትችለውን መጠነ ሰፊ ጥቃት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተገንዝቦና ሁሉም ነቅቶ ለመጠበቅ የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት እንላለን።

በእኛ በኩል ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት በአማራውና በኦርቶዶክስ ክርሲትያን አማኞች ላይ ለሚደርሰውና እየደረሰም ስላለው ጥቃት፣ መንግሥታዊ መዋቅርን በመጠቀም ህወሀትና ኦነግ እያደረሱ ያሉትን የዘር ጭፍጨፋ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ ለተባበሩት መንግሥታት፣ ለአውሮፓ ኅብረት፣ የሰው ልጅ መብት እንዲከበር ለሚሠሩ ድርጅቶች እንዲሁም ለታላላቅ መንግሥታትና ፓርላማወቻቸዉ ማሳወቁን በርትተን እንደምንቀጥልበት እናሳውቃለን።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሁሉም አገራችን ያለችበትን ሁኔታ የሚያሳስበው ሁሉ በአንክሮ እንዲገነዘበው የምንፈልገው፣ ኢትዮጵያ አገራችን ከገባችበት አዘቅት እንድትወጣ ህወሀት አብረን እንድንኖር ሳይሆን፣ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል በተንኮል የቀረጸችው መርዘኛ ህገመንግሥት በአዲስ ሳይለወጥ፣ እንዲሁም የዜጎችን መብት ያበላለጠው የክልል አወቃቀር ፈርሶ በፌደራል ክፍለ ግዛቶች አወቃቀር ሳይተካ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እንደማይሰፍን ነው።

ከምርጫ በፊት አዲስ ህገ መንግስት ማዘጋጀት የግድ ነዉ እንላለን። ይህንን የመሳሰሉ ዋና ዋና በሆኑ የአገር ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ መፍትሄ ለማምጣት ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ የመግባባት ኮንፈረንስ መንግሥትና ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በጋራ በመሆን እንዲያዘጋጁ ጥሪ እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ ሉዐላዊነቷን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኖራለች

ቸሩ አምላካችን ኢትዮጵያንና ህዝቧን በሰላም ይጠብቅ